ኢትዮጵያ

# የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን አባላት የአሰራር እና የስነ-ምግባር መመሪያ

ጥር 2015 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በሽግግር ሂደት ውስጥ ያለፈች ቢሆንም በፖሊሲ የተመራ የሽግግር ፍትህ ሂደት ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ ውጤታማ የሆነ የሽግግር ሂደት ማድረግ ያልተቻለ በመሆኑ፣

ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሀገራችን የሽግግር ፍትህ ሂደት በምን አግባብ መመራት አለበት የሚለውን እና መሰል ጥያቄዎችን የሚመልስ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ለማዘጋጀት በፍትህ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የባለሙያዎች ቡድን ተደራጅቶ እንቅስቃሴ የጀመረ በመሆኑ፣

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የተለያዩ የዝግጅት ምዕራፎች ያሉት፣ ሰፊ የህዝብ እና የባለሙዎች ምክክር የሚጠይቅ፣ የመደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የሚዲያ አካላት ሽፋን የሚኖረው እና የተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሂደቱ በተለያየ መልኩ ተሳትፎ የሚያደርጉ በመሆኑ፣

በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የሚሳተፉ ባለሙያዎች በዝግጅት ሂደቱ፣ በሚዘጋጁ የተለያዩ የምክክር መድረኮች፣ ከተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋር ከሚኖር ግንኙነት እና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ከሚፈጠር ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሊከተሉት የሚገባቸውን የሥነ ምግባር መርሆ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን ይህን የአሰራር እና የስነ-ምግባር መመሪያ አዘጋጅቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ''የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን አባላት የስነ-ምግባር መመሪያ'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ፖሊሲ"** ማለት በፍትህ ሚኒስቴር ስር የተደራጀው የባለሙያዎች ቡድን የሚያዘጋጀው ረቂቅ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ነው፤
2) **"የባለሙያዎች ቡድን"** ማለት በፍትህ ሚኒስቴር ስር የሽግግር ፍትህ ረቂቅ ፖሊሲ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ የተደራጀ ከተለያዩ አካላት የተውጣጣ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን ነው፤
3) **''የባለሙያዎች ቡድን አባል''** ማለት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን አባል እንዲሆን በፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር የተሰየመ ሰው ነው።
4) **"ሚኒስቴር"** ማለት የፍትህ ሚኒስቴር ነው፤
5) **"የበላይ አመራር"** ማለት የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ወይም የመንግስት ሕግና ፍትህ አገልግሎት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ነው፤
6) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ነው፤
7) **''ስትራቴጂ''** ማለት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ዝግጅት የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ ነው፤
8) ሚዲያ በስትራቴጂው የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤
9) በወንድ ፆታ የተመለከተው አገላለፅ የሴትንም ፆታ ያካትታል።

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ የባለሙያዎች ቡድን አባላት ከፖሊሲው ዝግጅት ስራ ጋር በተያያዘ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. **የመመሪያው ዓላማ**

የመመሪያው ዓላማ የባለሙያዎች ቡድን አባላት በፖሊሲ ዝግጅት የተለያዩ ሂደቶች፣ በሚዘጋጁ የምክክር መድረኮች፣ ከሚዲያ አጠቃቀም እና ከሚዲያ አካላት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት እና መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ከሚኖር ግንኙነት ጋር በተያያዘ ሊከተሉት የሚገባውቸውን የስነ-ምግባር መመሪያዎችን ማስቀመጥ ነው።

## ክፍል ሁለት

## የስነ ምግባር መርሆዎች

5. **በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የስነ-ምግባር መርሆዎች**

ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የፖሊሲ ዝግጅት ሂደት ማለት የምክክር መድረኮችን ጨምሮ በባለሙያዎች ቡድኑ አባላት የሚከናወን ሰነድ የማዘጋጀት፣ በተዘጋጀ ሰነድ ላይ በአባላት መካከል የሚደረግ ውይይትን፣ ከፖሊሲው ዝግጅት ጋር በተያያዘ የባለሙያዎች ቡድኑ ከበላይ ሀላፊ ጋር የሚያደርገው ውይይት እና የባለሙያዎች በድኑ እንደ ቡድን ከተለያዩ ኤክስፐርቶች እና አጋር አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ውይይቶች ይጨምራል።

በፖሊሲ ዝግጅት ሂደት እያንዳንዱ የባለሙያዎች ቡድን አባል የሚከተሉትን የስነ-ምግባር መርሆዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡ -

1) ከፖሊሲ ዝግጅት ስራው ጋር በተገናኘ የበላይ ሀላፊ እና/ወይም የባለሙያዎች ቡድኑ ሰብሳቢ በሚጠራው ስብሰባ ላይ ሰዐት አክብሮ መገኘት አለበት፤
2) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ስብሰባ ጥሪ ሲደረግ ጥሪው ለባለሙያዎች ቡድን አባላት ቢያንስ ከሁለት ቀን በፊት እንዲያውቁት መደረግ አለበት፤ ጥሪው ስብሰባው የሚደረግበትን ሰዐት እና ቦታ መግለጽ ይኖርበታል፤
3) በማንኛውም ምክንያት ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው ስብሰባ ላይ መገኘት የማይችል አባል ይህንኑ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፤
4) ከፖሊሲ ዝግጅት ስራው ጋር በተገናኘ በበላይ ሀላፊ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ተገቢውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል፤
5) ከፖሊሲ ዝግጅት ስራው ጋር በተገናኘ በፈቃደኝነት ወይም በበላይ አመራር የሚሰጡ ስራዎችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አጠናቆ ያስረክባል፤
6) የባለሙያዎች ቡድኑ በሚያካሂዳቸው ውይይቶች እያንዳንዱ አባል የሌላውን አባል ሀሳብ ማድመጥ እና ማክበር አለበት፤
7) በባለሙያዎች ቡድን የሚከናወን ማንኛውም ተግባር ወይም የሚዘጋጅ ሰነድ ወይም የሚተላለፍ ውሳኔ ሁሉም የቡድኑ አባላት እንዲያውቀው ሲደረግ - በውሳኔው ይዘት በመመራት ስራዎችን ያከናውናል፤
8) በባለሙያዎች ቡድን ውይይት ወቅት የሀሳብ ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ በስምምነት እንዲያልፍ የተደረገውን ወይም በበላይ አመራር አቅጣጫ የተሰጠበትን ገዢ ሀሳብ ተፈጻሚ ይደረጋል፤

9) በፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱ ፕሮፌሽናሊስም የሚጠይቀውን ስነ-ምግባር ይከተላል፡ በተለይም የግል የህይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የብሄር እና የመጡበትን ተቋም አቋም ማንጸባረቅ የተከለከለ ነው፤

10) በስትራቴጂው የተቀመጡ ግዴታዎች እና ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የባለሙያዎች ቡድን አባል በፖሊሲ ዝግጅት ሂደቱ ሚስጢራዊነታቸው ሊጠበቅ የሚገቡ እና ጊዜያቸውን ሳይጠብቁ ለሶስተኛ ወገን ይፋ ቢደረጉ ያልተገባ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሰነዶች እና የተከናወኑ፣ እየተከናወኑ እና ሊከናወኑ የታቀዱ ተግባራትን ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

11) ማንኛውም የባለሙያዎች ቡድን አባል በፖሊሲው ዝግጅት ሂደት ያገኛቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ - በፖሊሲ ዝግጅት ወቅት - ሂደቱን የሚነቅፍ፣ የሚተች እና የባለሙያዎች ቡድኑን የቡድን መንፈስ ሊያውክ የሚችል ጽሁፍ በማንኛውም ሙያዊ መጽሄቶች (ጆርናል)፣ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች እና የህትመት ሚዲያዎች መጻፍ የለበትም፤ ሌሎች አካላት በማህበራዊ ሚዲያ ገጾቻቸው የጻፉትን ማጋራት የለበትም፤

12) ማንኛውም የባለሙያዎች ቡድኑ አባል የባለሙያዎች ቡድኑ የፖሊሲ ዝግጅት ስራውን ለማቀላጠፍ እንዲረዳው እየተጠቀመበት ባለው የቴሌግራም ቡድን ገጽ ወይም ወደፊት ሊጠቀምባቸው በሚችላቸው የመረጃ መለዋወጫ ገጾች ላይ ከፖሊሲ ዝግጅት ስራው ውጪ የሆኑ ጉዳዮችን ማጋራት የለበትም፤

13) ማንኛውም የባለሙያዎች ቡድኑ አባል የባለሙያዎች ቡድኑ የፖሊሲ ዝግጅት ስራውን ለማቀላጠፍ እንዲረዳው እየተጠቀመበት ባለው የቴሌግራም፣ የዋትስ አፕ፣ ኢሜይል ወይም ማንኛውም የመረጃ መለዋወጫ ገጽ ላይ የሚለቀቁ መረጃዎችን የመከታተል፣ እና ግብረ-መልስ ለሚፈልጉ ጉዳዮች ጊዜውን የጠበቀ ምላሽ መስጠት አለበት፤

14) ማንኛውም የቡድኑ አባል በተለያየ ምክንያት ከባለሙያዎች ቡድን አባልነት ሲወጣ ከፖሊሲ ዝግጅት ስራው ጋር በተገናኘ በእጁ የሚገኙ ሰነዶችን ለባለሙያዎች ቡድኑ ሰብሳቢ ማስረከብ አለበት።

## 6. በምክክር መድረኮች ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የስነ-ምግባር መርሆዎች

ከላይ የተመለከቱ የስነ-ምግባር መርሆች እንደተጠበቁ ሆኖ - በአዲስ አበባ እና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚደረጉ የፖሊሲ ግብዐት ማሰባሰቢያ የምክክር መድረኮች - እያንዳንዱ የባለሙያዎች ቡድን አባል የሚከተሉትን የአሰራር እና የስነ-ምግባር መርሆዎች ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡ -

1) ለምክክር መድረክ ጽሁፍ የሚያቀርብ ወይም ሌላ ተዛማጅ ሀላፊነት የተሰጠው የባለሙያዎች ቡድን አባል ለመድረኩ በሚመጥን ደረጃ ቀድሞ ተዘጋጅቶ መገኘት፡ ማቅረብ ወይም አገልግሎቱን መስጠት አለበት፤

2) እያንዳንዱ የባለሙያዎች ቡድን አባል ለምክክር መድረኩ መሳካት በበላይ ሀላፊ ወይም በቡድኑ የተሰጠውን ሃላፊነትን ተቀብሎ በአግባቡ መወጣት አለበት፤

3) እያንዳንዱ ምደባ የተሰጠው የባለሙያዎች ቡድን አባል የምክክር መድረክ በሚከናወንበት ዕለት ተሳታፊዎች እንዲገኙ ከተመቀጠው ጊዜ ቀድሞ መገኘት አለበት፤

4) እያንዳንዱ የምክክር መድረክን ውይይት የሚመራ ወይም የሚያሳልጥ የባለሙያዎች ቡድን አባል በምክክር ፍኖተ-ካርታው ላይ በተመለከተው መሰረት ተሳታፊዎችን በእኩል ማየት እና እያንዳንዱ ተሳታፊ የሚሰጠውን ሀሳብ ማድመጥ እና ማክበር አለበት፤

5) የምክክር መድረኩን እንዲመራ ወይም እንዲያሳልጥ የተመደበ የባለሙያዎች ቡድን አባል በምክክር ፍኖተ-ካርታው ላይ በተመለከተው መሰረት ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን ባልተገደበ መልኩ እንዲገልጹ ማበረታታት አለበት፤ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን በአግባቡ መግለጽ የሚችሉበትን ቋንቋ ለመጠቀም ሲፈልጉ ማበረታታት አለበት፤

6) በባለሙያዎች ቡድኑ ስብሳቢ ወይም የምክክር መድረክ እንዲመራ ወይም እንዲያሳልጥ በተመደበ የባለሙያዎች ቡድን አባል ለተሳታፊዎች ጥሪ ሲተላለፍም ሆነ በውይይቶች ሂደት የተሳታፊዎች የትምህርት፣ የማህበራዊ፣ የባህላዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ወታደራዊ እና ሌሎች ማዕረጎች በአግባቡ መጠቀስ አለባቸው፤ አግባብነት ያላቸው የመስተንግዶ እና የፕሮቶኮል ስነ-ስርዐቶች ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል።

7. **መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በሚደረግ ግንኙነት ተግባራዊ ሊደረጉ የሚገባቸው የስነ-ምግባር መርሆዎች**

በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት ሂደት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ መመሪያ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡ -

1) ማንኛውም የባለሙያዎች ቡድን አባል ከፖሊሲ ዝግጅት ስራው ጋር በተገናኘ የበላይ አመራር ወይም የቡድን መሪውን ይሁንታ ሳያገኝ መንግስታዊም እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ግንኙነት መፍጠር አይችልም፤

2) ለፖሊሲ ዝግጅት ስራው ሲባል ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በተፈጠረ ግንኙነት እንዲያስተባብር ወይም ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ሀላፊነት የተሰጠው የባለሙያዎች ቡድኑ አባል እንዲያስተባብር ወይም እንዲያመቻች ከተባለው ጉዳይ ውጪ ሌሎች የግል ወይም የመጣበትን ተቋም ጉዳይ ማንሳትም ሆነ ማስፈጸም የለበትም፤

3) መንግስታዊም እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ለተፈጠረ ግንኙነት የማስተባበር ወይም ያመቻችነት ሚና የተጫወተ የባለሙያዎች ቡድን አባል ላከናወነው ተግባር ከተቋማቱ የዓይነትም ሆነ የገንዘብ ስጦታ ወይም ክፍያ መቀበል የለበትም።

4) የሚዲያ አጠቃቀም እና ከሚዲያ አካላት ጋር የሚኖር ግንኙነትን በሚመለከት በስትራቴጂው የተካተቱ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ተግባራዊ ይደረጋሉ።

**ክፍል ሶስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

8. **የመመሪያው የአፈፃፀም ሁኔታ**

ይህ መመሪያ ከሚኒስቴሩ ሌሎች መመሪያዎች እና የአሰራር ሥርዓቶች ጋር በተናበበ መልኩ ተፈፃሚ ይደረጋል።

9. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በበላይ አመራር ታይቶ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ፣ ጥር …… ቀን 2015 ዓ/ም**